# ከእነ "ኦክላንድ ተቋም" ተከታታይ ውንጀላዎች በስተጀርባ

**መሐሪ ይፍጠር**

yiftermehari@gmail.com

ሰሞኑን አይጋ ፎረም ድረ-ገፅ የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫን ጠቅሶ "ኦክላንድ" የተሰኘው አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ተቋም "ጊቤ ሳልሳዊን" (ጊቤ-ሶስትን) በተመለከተ ተከታታይ የሐሰት ፍብረካ ውንጀላዎችን ያለ አንዳች ማስረጃ ማቅረቡን አስነብቦናል። የጉዳዩን አስገራሚነት አስመልክቶ "የእብደት ማለት አንድን ነገር በተመሳሳይ መንገድ ደግሞ ደጋግሞ ሞክሮ አንድ ዓይነት ውጤት ማግኘት ነው" የሚለውን የታዋቂውን የሳይንስ ሊቅ የአልበርት አንስታይን አባባል የጠቀሰው የሚኒስቴሩ መግለጫ፤ "ኦክላንድም" ይሁን እንደ ሂዩማን ራይትስ ዎች ዓይነት ሌሎች በሰብዓዊ መብት ስም የራሳቸውን የርዕዮተ-ዓለም ቀኖናን የሚያቀነቅኑ ኃይሎች ተመሳሳይና እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ የሪፖርት ጋጋታ እንደሚያኻኅደጉዱ ገልጿል።

እነዚህ ሪፖርቶችም የአሜሪካና የእንግሊዝ እንዲሁም ሌሎች የልማት አጋር ሀገራት ቡድን (DAG) የመስክ ጉብኝቶችንና ያገኟቸውን ትክክለኛ ውጤቶች የማይቀበሉ፣ ከፍ ሲልም የአጋር ሀገራቱን ቡድን የእነርሱን የጥንቆላ ድምዳሜ ስላልተቀበለ እስከማጣጣል መድረሳቸውን መግለጫው ያትታል። እርግጥ "ኦክላንድም" ይሁን ሌሎች የሰብዓዊ መብት ካባን ደርበው የሚያቀነቅኑ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎች ሀገር ውስጥ የሚገኙትን እንደ አሜሪካው የልማት አጋር (USAID) እንዲሁም የእንግሊዙ የልማት ደጋፊ (DfID) ያሉትንና በተጨባጭ ጊቤ-ሶስትን ቦታው ድረስ በመሄድ ቃኝተው መሬት ላይ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በማጣራት እ.ኤ.አ. በጥር ወር 2012 ዓ.ም "የሰብዓዊ መብት ጥሰትን አላየንም" በማለት ያወጡትን ትክክለኛ ሪፖርት ከመቀበል ይልቅ፤ ውጭ ሆነው በራሳቸው የርቀት መቆጣጠሪያ መሳሪያ (Remot Control) ውሸት እየተመሩ የቀመሩትን አሉባልታ በመደጋገም በግድ "እኛ ያልነውን ካልተቀበላችሁ ሞተን እንገኛለን" የሚሉ ናቸው። ያለ አንዳች አስረጅ።

ግና እዚህ ላይ ከእነ "ኦክላንድ" ተቋም ተከታታይ የሐሰት ውንጀላዎች በስተጀርባ ያለው እውነት ምንድነው? ብለን መጠየቅ ያለብን ይመስለኛል። አዎ! የዚህ ፅሑፍ ዓላማም ይህን ሃቅ ለውድ አንባቢዎቼ በግልፅ በማሳየት የ"ኦክላንድን" እና ሌሎች ከማንነታቸው ጋር የማይተዋወቀውን የሰብዓዊ መብት ደበሎን ለብሰው በሐሰት የሚያዳምቁ ፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎችን በቅጥፈት የታጀቡ የቅብብሎሽ ድርሳናትን ገላልጦ እርቃናቸውን ማስቀረት ነው።

እንደሚታወቀው “ጊቤ ሳልሳዊ” የኤሌክትሪክ ማመንጫ ግድብን አስመልክቶ ያልተባለና እንዲባል ያልተደረገ እንዲሁም ያልተነገረና እንዲነገር ያልተደረገ በሐሰት ያልተቀናበረ የቅብብሎሽ ዘመቻ የለም። የዘመቻው መሪ ተዋንያን ራሳቸውን ሂዩማን ራይትስ ዎች፣ ፍሬንድስ ኦፍ ሌክ ቱርካና፣ ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ፣ አምንስቲ ኢንተርናሽናል፣ ኦክላንድ ኢንስቲትዩት…ወዘተርፈ እያሉ የሚጠሩ የፖለቲካ ቡድኖች ናቸው። ታዲያ የእነዚህ አክራሪዎች ተደጋጋሚና አሰልቺ ሪፖርት የረጅም ልቦለድ ድርሰት ባህሪ የሚታይበት ሲሆን፣ የሃቅ እጥረት ያለበት መሆኑ ግን የአደባባይ ምስጢር ነው። ምክንያቱም ሁሉም የሚያስቡት በጥርጣሬ ላይ የተመሰረተውና ማስረጃ አልቦ ቅብበሎሻዊ ሪፖርታቸው “ውሸት ሲደጋገም እውነት ይመስላል” የሚለው የቆየ የፕሮፖጋንዳ ስልት ዛሬ ላይም የሚሰራ ስለሚመስላቸው ነው። ያም ሆነ ይህ ግን ከእነ “ኦክላንድ” ተቋም ተከታታይ ውንጀላ በስተጀርባ ያለውን ዕውነት መመልከት የግድ ይላል።

1870 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም እንደሚኖረው የሚጠበቀውና የህዳሴያችን ሌላኛው ብርሃን ፈንጣቂ የሆነው እንዲሁም በአሁኑ ወቅት ስራው ከ70 በመቶ በላይ መጠናቀቁ የሚነገርለት ሳልሳዊ ጊቤ፤ በ“ኦክላንድ” ተቋምና በመሰሎቹ ያው እንደተለመደው የታዳጊ ሀገራትን የተፋጠነ ልማታዊ ጉዞ ማደናቀፊያ ሰበባ አስባብ ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል– ምንም እንኳን ድርጊቱ የኬንያንና የኢትዮጵያን መንግስትና ህዝቦችን እጅ የመጠምዘዝ አቅም ባይኖረውም፡፡ በኦሞ ወንዝ ላይ በመገንባት ላይ የሚገኘው ይህ ግድብ፤ በኢትዮጵያና በኬንያ መንግስታት የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ባደረገ መልኩ በተደረሰ ስምምነት በመከናወን ላይ የሚገኝ ፕሮጀክት ነው፡፡ ምንም እንኳን ኢትዮጵያዊያኑ ሙርሲዎችና ኛንጋቶሞች የሚገኙበት ኦሞ ወንዝ ለኬንያው የቱርካና ሐይቅ ገባር ቢሆንም፤ እነ “ኦክላንድ” ተቋም እንደሚያስወሩት በወንዙ ላይ የሚገነባው “ጊቤ- ሦስት” በሐይቁም ይሁን በአካባቢው በሚኖሩ “ቱርካናዎችና ኛንጋቶሞች” ላይ የሚያስከትለው አንዳችም ተፅዕኖ የለም፡፡

ከዚህ ይልቅ በአካባቢው ለሚገኙ ህዝቦችና ለቱርካና ሐይቅ የጎላ ጠቀሜታ ያለው እንዲሁም ቀደም ሲል የነበረውን የሁለቱን ሀገራት የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት ይበልጥ የሚያጠናክረው መሆኑን የተለያዩ ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡ ምንም እንኳን ጽንፈኛ ተቋሞቹ “… የግልገል ጊቤ - ሦስት ፕሮጀክት በአካባቢው ህዝብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳርፋል” እያሉ ሊቀሰቅሱ ቢሞክሩም፤ ተጨባጭ ዕውነታው ግን ይህ አይደለም፡፡ የግድቡ መገንባት ህዝባዊም ይሁን ስነ-ምህዳራዊ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን ለመግለፅ ጠቀሜታው ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም፡፡ ይሁንና ጥቂት ዋና ዋና አብነቶችን ለመጥቀስ ያህል የግድቡ መገንባት፤ የአካባቢው ህዝብ ከከብት እርባታ በተጨማሪ በአሳ ማስገርና በመስኖ ልማት እንዲጠቀም የሚያስችል ከመሆኑም በላይ፤ እጅግ ኋላ ቀር በሆነው በዚያ አካባቢ ትምህርት ቤት ፣

ሆስፒታል፣ መንገድና ኢንቨስትመንትን የመሳሰሉ የመሰረተ - ልማትና የንግድ ስራዎች እንዲካሄዱ ዕድል ይፈጥራል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም፤ ለዘመናት የብርሃን ጭላንጭል አይቶ የማያውቀው የአካባቢው ህዝብ የኤሌክትሪክ ኃይል ሰለሚያገኝ በአኗኗር ዘይቤው ላይ ለውጥ ያመጣል፤ ቀደም ሲል በውኃ ሙላት ይጥለቀለቁ የነበሩት ህዝቦችን ህይወት ለመታደግም የግድቡ መገንባት ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ እንግዲህ ሌሎቹ ቀርተው እነዚህ በጣት የሚቆጠሩ ጠቀሜታዎች ብቻ የአክራሪዎቹን የፈጠራ "አሉታዊ ተፅዕኖን" እርቃኑን የሚያስቀሩት ናቸው፡፡ ታዲያ የጥቅሞቹ ተቋዳሾች በወንዙ አካባቢ የሚገኙት ኢትዮጵያዊያኑ ኛንጋቶሞችና ሙርሲዎች ብቻ አይደሉም፡፡ ኬኒያዊያኑ ቱርካናዎችም ከግድቡ መገንባት ተጠቃሚዎች ናቸው፡፡ ይህም ግድቡ በአካባቢው የሚገኙትን ሁሉንም ህዝቦች ወደ ተሻለ ህይወትና የልማት አቅጣጫ የሚወስድ መሆኑን ያመላክታል፡፡

በሚያስገርም ሁኔታ ለህዝቦች ተቆርቋሪ በመምሰል መልሰው የህዝቦችን ልማታዊ እመርታ በፈጠራው ወሬ ለማኮላሸት የሚሯሯጡት እነዚህ አክራሪ ኃይሎች፤ "...የግድቡ ግንባታ የቱርካና ሐይቅን ህልውና አደጋ ላይ ይጥላል፣ የእንስሳትንና ዕፅዋቶችን ጥናት ለማካሄድ ስለሚያስቸግር ኢትዮጵያ ለሐይቁ ደህንነት ማሰብ አለባት..." በማለት ያቀረቡት አምክንዮ ውኃ የሚቋጥር አይደለም፡፡ ለምን ቢሉ፤ ዕውነታው በፍጹም ከፈጠራ ታሪኮቻቸው ጋር የተገናኘ ባለመሆኑ ነው፡፡ እርግጥም ሳልሳዊ ጊቤ በቱርካና ሐይቅ ላይም ይሁን በአካባቢው ሥነ-ምህዳር ላይ የሚያስከትለው አንዳችም ጉዳት የለም። ምክንያም የግድቡ መሰራት በየጊዜው በመዋዠቅ የሚታወቀውን የቱርካና ሐይቅ ፍሰት ወጥነት እንዲኖረው እንዲሁም ትነቱ እንዲቀነስና የውኃው መጠንም እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ ይሁንና አክራሪ ኃይሎቹ ከዚህ ሃቅ ተገላቢጦሽ በሆነ ሁኔታ ያለሃፍረት "ዓይኔን ግንባር ያድርገው" በማለት፤ የግድቡ መገንባት የቱርካናን ውኃ በ12 ሜትር እንደሚቀንሰው ያለ አንዳች ማስረጃ ይከራከራሉ፡፡

የግድቡ መገንባት ለቱርካና ሐይቅ ጠቃሚ እንደሆነና ሀገራቸው ያለባትን የኃይል እጥረትንም በአጭር ጊዜ ውስጥ በመቅረፍ ህዝባቸውን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ እምነታቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ታዲያ ሌላው ቢቀር ከዚህ ጉዳዩ ከሚመለከተው ቡድን ውጪ ከቶ ማን እማኝና ምስክር ሊሆን ይችላል?–ማንም። ግና እኔ እስከሚገባኝ ድረስ በግድቡ ግንባታ የሚጎዱት በአካባቢው የሚኖሩት ህዝቦች ወይም የቱርካና ሃይቅ አይደሉም–እኚሁ በሰብዓዊ መብት ሽፋን ተጠልለው "የዕለት እንጀራቸውን" በማብሰል ላይ ያሉት ፅንፈኛ አክራሪ ቡድኖች እንጂ። እናም እነዚህ ሃይሎች ሰሚ ጆሮ ኖሯቸው 'እንዴት?' የሚሉ ከሆነ፤ ዕውነታው እንዲህ የሚነበብ ነው።...

…እንደሚታወቀው “ለህዝቦች ሰብዓዊ መብት እንሟገታለን፣ ግጭቶችን እንፈታለን…ወዘተ” በሚል የሽፋን ስም ተደራጁት እንደ “ኦክላንድ” ተቋም፣ ሂዮማን ራይትስ ዎች፣ ኢንተርናሽናል ክራይስስ ግሩፕ… ወዘተ. የመሳሰሉት አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ኃይሎች፤ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ዕድገታቸውን በተገቢው ደረጃ ካረጋገጡ እነርሱ በሽፋንነት የተደራጁበት ሚናቸው ተፈላጊ እንደማይሆን ጠንቅቀው ያውቁታል። ምክንያቱም ሀገራቱ የተፈጥሮ ፀጋዎቻቸውን ተጠቅመው የዕድገት ማማን በከፍተኛ ደረጃ መቆናጠጥ ከጀመሩ፤ እንከራከርለታለን የሚሉት ሰብዓዊ መብት፣ እንፈታቸዋለን የሚሏቸው ግጭቶች… ወዘተርፈዎች ከዕድገቱ ጋር ተያይዞ በሚመጣ ለውጥ ችግርነታቸው ስለሚያከትም፤ የተከናነቡት የውሸት ጭምብል መገፈፉ ስለማይቀር ነው፡፡

ይህም ከድብቅ የፖለቲካ አጀንዳቸው ባሻገር፤ በሰብዓዊ መብትና በግጭቶች ሰበብ ቀደም ሲል ወደ ኪሳቸው ይገባ የነበረው ረብጣ ዶላር እንዳይኖር ስለሚያደርግ ጥቅማቸውን ክፉኛ ያጎዳዋል፡፡ ታደያ ይህ ጥቅማቸው እንዳይቀር ከሰው ልጅ ክቡር ህይወት ይልቅ ለቢራቢሮና ለግዑዛን ፍጥረታት ህልውና በማላዘን ሀገራቱ ዕድገታቸውን እንዳያሳልጡ የልማት ጋሬጣ በመሆን ፊት ለፊታቸው ይገተራሉ፡፡

ታዲያ ይህን ሃቅ “ከጊቤ-ሦስት” አኳያ ስንመለከተው፤ በግድቡ መሰራት ሳቢያ ኢትዮጵያዊኑ ኛንጋቶሞችና ሙርሲዎች እንዲሁም ኬንያዊያኑ ቱርካናዎች የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ መሆናቸው አይቀርም፡፡ ይህም የአካባቢው ህዝቦች በመሰረተ - ልማትና በሌሎች መሰረታዊ አገልግሎቶች ሳቢያ ዓይናቸውን በመክፈት የአኗኗር ዘይቤያቸውን እንዲቀይሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ህይወታቸውን ከዚህ በፊት ከነበረው በተለየ ሁኔታም መምራት ይጀምራሉ፡፡ የሰብዓዊ መብት ጥቅምን ስለሚገነዘቡም ቀደም ሲል በግጦሽና በውኃ ምክንያት ከሚጋጯቸው ህዝቦች ጋር በሠላም ተከባብረው ይኖራሉ፡፡ እርግጥም አንድ ህዝብ ከዕድገት ጋር ተያይዞ በሚፈጥረው ሚዛናዊ እሳቤ ስለ ሰብዓዊ መብትም ይሁን ስለ ግጭት አፈታት በቂ ግንዛቤ ከያዘ ፤ ለሰብዓዊ መብት እሟገታለሁ የሚል ድርጅትም ሆነ ግጭት ፈቺ ተቋማት አያስፈልጉም፡፡ ከልማቱ ጋር በሚዳብር ንቃተ - ህሊና የተመቻቸ አካባቢና የቅርስ ጥበቃ አስተሳሰብ መጎልበቱ ስለማይቀር፤ የአካባቢ ተንከባካቢ ድርጅትም ተፈላጊነት የለውም። እናስ ውድ አንባቢዎቼ ምን ትላላችሁ?—በእነዚህ ሃቆች ሁሉ ሳቢያ የሳልሳዊ ጊቤ መገንባት አደጋው ከአካባቢው ህዝቦችና ስነ-ምህዳር ይልቅ ለአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ተቋሞች አይደለምን?—እንዴታ!—በቃ የመረረው የበስተጀርባ ሃቅ ይኸው ነው። እንግዲህ ‘ጆሮ ያለው ይስማ!’ ማለት ይሄኔ ይመስለኛል።

ታዲያ እዚህ ላይ ‘ሃቁ ግድቡ ህዝቦችን በልማት ተጠቃሚ እንደሚያደርግ መሆኑ እየታወቀ፤ ጽንፈኞቹ ለምን ይዋሻሉ?’ የሚል ጥያቄ ስናነሳ፣ ምላሹ ሁለት ፖለቲካዊ ጉዳዮች ሆነው እናገኛቸዋለን። አንድም እነዚህ ኃይሎች ከኒዮ- ሊበራል አስተሳሰብ ውጪ በራሳቸው ነባራዊ

ሁኔታ ለማደግ ደፋ ቀና የሚሉ ሀገሮችን ለመድፈቅ የሚያደርጉት ትዕይንት ሲሆን፣ ሁለትም ይህ ተግባራቸው ካልተሳካላቸው ሀገራቱን በቀለም አብዮት በማመስ ለእነርሱ የሚያጎነብስ አሻንጉሊት መንግስት መመስረት ነው– ከሪፖርት ጋጋታቸውና ከሐሰት ውንጀላቸው በስተጀርባ ያሉት ሌላኛዎቹ ዕውነተኛ ፍላጎታቸው። እስቲ ለማንኛውም ሁለቱንም ጉዳዮች በጥምረት ጥቂት ፈታ አድርገን እንመልከታቸው።

እንደሚታወቀው አክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች ርካሽ ጉልበት፣ ያልተበላ ድንግል መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን ከታዳጊ ሀገራት የመመዝበር ሱስና በሰው ሃብት የመበልፀግ ህልም አላቸው፡፡ እናም ለመልማትና ለመንቃት የሚወተረተሩ ህዝቦችን ለመደፍጠጥ ተኝተው አያድሩም፡፡ የለማና የሰለጠነ ህዝብ ለመገዛት ስለማያጎነብስ ያን ስጋት ከወዲሁ ለማምከን ይዋትታሉ፡፡ ስለሆነም ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ታዳጊ ሀገራት እያስመዘገቡት ያለው ፈርጀ ብዙ የልማት እመርታ፤ ካረጀ ካፈጀው የፖለቲካ ንግዳቸው ጨርሶ ስለሚያወጣቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰትና የአካባቢ ጥበቃ ጭንብልን አጥልቀው ፕሮጀክቶችንና የልማት ስራዎችን ያውግዛሉ፡፡ የሆዳቸውን በሆዳቸው አድርገው፤ “ይቺ ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም” ይላሉ፡፡ ከቻሉም የቀለም ወይም የፍራፍሬ ምናምን አብዮት በማቀጣጠል ታዳጊ ሀገራትን ለመለብለብና ለማስለብለብ ይተጋሉ፡፡ ይህን የሚያደርጉበት ነባራዊ ምህዳር በሀገራት ውስጥ ከሌለ ደግሞ የሀገራቱን መልካም ገፅታ በቅጥፈት በሚለውሱት የኒዮ - ሊበራሊዝም አስተሳሰብ አቀንቃኞች አማካኝነት ታዳጊ ሀገራትን ከለጋሽ ሀገራትና ተቋማት ጋር ለማቆራረጥ አቅደው ይሰራሉ፤ ይማፀናሉ፤ ይማልዳሉ፡፡

ፍላጎታቸውና ድብቅ አጀንዳቸው ይኸው ነው። እርግጥም ስውሩ ህልማቸው ይህ ባይሆን ኖሮማ፣ የሁለቱን ሀገራት ከብትና አሳ እርባታ ይበልጥ ለማዘመን እንዲሁም በዘመናት ያለ ምንም መሰረተ ልማት ሲማቅቅ የኖረው ህዝብ የመኖሪያ አካባቢው እንዲለማ፣ ትምህርት ቤት፣ ጤና፣ መንገድ፣ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ግዙፍ ዕድል ይዞ የሚመጣውን የግቤ ሶስት ፕሮጀክትን ባልተቃወሙ ነበር፡፡ ለሰው ልጆች በተለይም ለጥቁር ጭቁን ህዝቦች ልዕልና የቆሙ የአምላክ ታናሽ ወንድም መስለው ለመታበይ ምንም የማያፍሩት የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል አላዛኞች፤ የሳልሳዊ ግንባታ በየጊዜው በመዋዠቅ የሚታወቀውን የቱርካና ሐይቅ ፍሰት ወጥነት እንዲኖረው እንዲሁም ትነቱ እንዲቀነስና የውኃው መጠንም እንዲጨምር እንደሚያደርግ እያወቁ፤ የቱርካና ሃይቅን ህልውና ጥያቄ ውስጥ እንደሚከተው በማስመሰል ባልተናገሩ ነበር፡፡ ይህ ብቻም አይደለም። ቀደም ባሉት ጊዜያት በውኃ ሙላት ይጥለቀለቁ የነበሩት የአካባቢው ህዝቦችን በመታደግ ረገድ ያለውን ጠቀሜታ እየተረዱም በባህር ማዶዋዊ ቅኝት ብዝሃ ህይወትን ያዛባል፣ የቱርካና ሃይቅን መጠን ይቀንሳል እያሉ ባልደሰኮሩ ነበር። ሌላ ሌላም…

ለነገሩ እነ "ኦክላንድ" ተቋም እውነታውን እንዲነግሩን አይጠበቅባቸውም፡፡ የቀጠርናቸው እኛ አይደለንምና። ምክንያቱም ቀጣሪያቸው የርዕዮተ-ዓለሙን ጣጣ በግምት አሊያም በጥንቆላ መልክ እንዲያወራርዱለት የሚከፍሏቸው እነ ጆርጅ ሶሮስ በመሆናቸው ነው። እኛም ከእነርሱ ሃቅን እንደማንጠብቅ፣ እነርሱ የሚያወሩትን እንደማናምን፣ እንደማናምን ብቻም ሳይሆን ውሸት በመሆኑ እንደምናወግዛቸው በሚገባ ይረዳሉ፡፡ በዚያ ላይ የመርህና የእንጀራ ጉዳይ መሆኑን ጠንቅቀን እንደምንረዳም ይገነዘባሉ፡፡ እናም እውነታው አይጥማቸውም፡፡…እናም "የኦክላንድ" ተቋም ተመሳሳይ የግልገል ጊቤ አዲሱ ሪፖርት ደራሲና መሰሎቻቸው ኮምፒውተራቸው ላይ ቁጭ ብለው ሃቅን እየሰረዙና እየደለዙ ይፅፋሉ።…ፅፈውም መልሰው በማላዘን "ዳቧቸውን" ይጋግራሉ።…

እርግጥ እነ "ኦክላንድ" ተቋም ለሃቅ የቆሙ፣ ለሰው ልጅ ልዕልና እና ለዓለማች ደህንነት የምር ተቆርቋሪ ቢሆኑ ኖሮ፤ ኬንያዊንና ኢትዮጵያዊያን ያለምንም ማቅማማት፣ አለማቅማማት ብቻም ሳይሆን በከፍተኛ ጉጉት የሚጠብቁትን ፕሮጀክት ግንባታ ለመቃወም ዘመቻ ባልከፈቱ ነበር፡፡ የግድቡ ግንባታ ማንንም የማይጎዳ ይልቁንም የሁለቱን ሀገራት ህዝቦች የሚያስተሳስር መሆኑን በጥናታቸው ካረጋገጡት የለጋሽ ሀገራት አማካሪ ቡድኖች እና ዲፕሎማቶች ድምዳሜ ባላፈነገጡ ነበር፡፡ አዎ! የሆድ ነገር ሆድ ይቆርጣል ነውና ብሂሉ ሆዳቸው ህሊናቸውን ድል ነስቶት ከቅጥፈት ጎን ሊሰለፉ ችለዋል፡፡

ያም ሆነ ይህ ግን የግቤ ሳልሳዊ ግድብ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫን እነ "ኦክላንድ" ተቋም ያልተገባ፣ ነገር ግን ቋት የማይሞላ የኒዮ - ሊበራሊዝም አስተሳሰብ ትርፍን ለማግበስበስ በመቋመጥ ብቻ እውነታውን በጥሞና ለማስተዋል ባለመፈለግ ወይም እያወቁ በሃፍረት ግድቡ ለኬንያዊኑ ቱርካናዎችና ለኢትዮጵያዊያኑ ሙርሲዎችና ኛንጋቶሞች የነገ ስጋት እንደሚሆን አድርጎ ሽብርን ለመንዛት መውተርተራቸው አዋጭ ብልሃት አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ዛሬ የሚያመዛዝን፣ ገለባውን ከፍሬው የሚለይ እንጂ፤ እነርሱ እንደሚያስቡት በፍሬ አልባ ዲስኩር ወዲያና ወዲህ የሚዘም አፍሪካዊ ትውልድ ባለመኖሩ ነው፡፡

የዚህ ፅሑፍ አንባቢ እንደሚገነዘበው ኢትዮጵያ ግድቡን ለመገንባት ስትነሳሳ ፕሮጀክቱ በቀጣናው ላይ የሚያስከትለው ችግር የሚኖር ከሆነ በማለት ሰፊ ጥናት አድርጋለች፡፡ የቱርካና ሃይቅም ይሁን ፕሮጀክቱ የሚያካልለው አካባቢ ብዝሃ- ህይወት እንዳይናጋ የሰከነ ጥናት ተደርጓል፡፡ ለጋሽ ሀገራትን ጨምሮ "ያገባናል፣ ይመለከተናል" የሚሉ ሁሉ ስፍራው ድረስ ተጉዘው ያለ አንዳች ማቅማማት ፕሮጀክቱ ችግር አልባ መሆኑን ለመቀበል የወሰኑት ኢትዮጵያ አስገድዳቸው እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ ሌላው ቢቀር ፕሮጀክቱ አንዳች ጥፋት የሚያስከትል ቢሆን ኖሮ፤ የኬንያ መንግስት የግድቡ ግንባታ ዋነኛ ተባባሪ አካል ባልሆነም ነበር፡፡ እንግዲህ ሃቁ ይህ ነው፡፡ እርግጥም ግድቡ ኬንያና ኢትዮጵያ ለጋራ ተጠቃሚነት ተስማምተው ወደ ተግባር የለወጡት ታላቅ

ልማት ነው፡፡ በምንኖርበት የዘመኑ ግሎባላይዜሽን ዓለም ውስጥ አብሮ የማደግ፣ በትብብርና በመደጋመጥ ለመኖር መስራት እንጂ፣ “እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል” የምንል ራስ ወዳድ ህዝቦች አለመሆናችንን አክራሪው ኒዮ-ሊበራል ሃይልም ቢሆን የሚገነዘበው ይመስለኛል፡፡ ባህላችንም ሆነ ሞራላዊ እሴታችን፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን መልካም ጉርብትናንና የጋራ ልማትን እንዲሁም እጅ ለእጅ ተያይዞ ማደግን የሚገልፅ ነው።

እናም ሀገራችን የዜጎቿንም ይሁን የወዳጅ ጎረቤቶቿን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ወይም አጥፊ የልማት ፕሮጀክት ትነድፋለች ብሎ መገመት ከመተዛዘብ ያለፈ ትርጉም አይኖረውም፡፡ ኢትዮጵያ እንኳንስ ለጎረቤቶቿ የማይመች ነገር ልትሰራ ቀርቶ ለቀጣናው፣ ለአፍሪካ ብሎም ለዓለም ሰላም መጠበቅ ያከናወነችውንና እያከናወነችው ያለችውን ተግባራት የ“ኦክላንድ” ተቋም አዲስ ሪፖርት መሳይ ድርሰት ከታቢው ጥቂት ከቀዩ ውስኪያቸው ዕረፍት ወስደው ወደ ኒውዮርክ ጎራ በማለት ጥቂት ማብራሪያ ቢወስዱ የሚጠቅማቸው ይመስለኛል። በመሆኑም አንዱን ድጦ ሌላውን የሚያነግስ የልማት ስራ አዋጭ ብቻ ሳይሆን፣ አደገኛ መሆኑን የሚረዳ ህዝብና መንግስት እንዳለን ከቶም ሊዘነጉት አይገባም፡፡ በሌላ አገላለፅ ፕሮጀክቱ የእኛዎቹ ሙርሲዎችና ኛንጋቶሞች እንዲሁም የኬንያዊያኑን ቱርካናዎች ህይወት የሚያለመልም እንጂ የሚያጨልም አይደለም፡፡

ሁላችንም እንደምናውቀው ኢትዮጵያና ኬንያ የቱርካናን ሃይቅ ተፋሰስና አዋሳኝ ሃብቶችን በተጠና እና በመግባባት የቀጣናውን የጋራ ተጠቃሚነት ሊያጎለብት የሚያስችል መርህና የፀና እምነት አላቸው፡፡ ታሪካችንም ሆነ ባህላችን በራሱ የሚያስተሳስረን ነው፡፡ ይህ የሁለቱ ሀገራት ትብብር በተባባሩት መንግስታት የአካባቢ ጥበቃ መርሀ-ግብር ተዋንያን ዘንድም ተቀባይነትንና አመኔታን ያስገኘ ፕሮጀክት ነው – ለዚህም ነው በጋራ ለመጠቀም እየተጋገዙ ግንባታውን ከፍጻሜ ለማድረስ እየሰሩ ያሉት፡፡ እናም እንደ “ኦክላንድ” ዓይነት ለህዝቦች ሰብዓዊ መብትና ለአካባቢ ተቆርቋሪ ነን ባይ ተቋማት ‘አንዱን ጥሎ ሌላውን አንጠልጥሎ’ እንዲሉ ለማምታታት ትበጀኛለች የሚሏትን የወሬ ቁጢት ብቻ እየመዘዙ በውል አልባ አሉባልታ ከብዥታ ያልወጡ ወገኖችን ለማወናበድ ቢወጡና ቢወርዱም ትርፋቸው ድካም ብቻ መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ እርግጥ እነርሱ ማውራት መብታቸው ነው፡፡ እኛም ያለማዳመጥ መብት አለን። የእነሱን ጉንጭ አልፋ ወሬ ያለማድመጥ ብቻ ሳይሆን፣ በተፈጥሮ ሃብቶቻችን የመጠቀም መብታችንም የተጠበቀ ነው፡፡

ዳሩ ግን ዛሬም ይሁን ነገ አንዳንድ ያደረ ሂሳብ አወራራጅ የፖለቲካል- ኢኮኖሚ ነጋዴዎች ጨርሰው አልጠፉም፣ አይጠፉምም፡፡ ይህ ነባራዊ እውነት ነው፡፡ ሁሉም ከራሱ ህቡዕ አጀንዳ በመነሳት የዓለምን መዘውር ወደ ፈለገበት አቅጣጫ ለማሾር የሚቋምጥ ኃይል መቼም ቢሆን መፈጠሩ አይቀሬ ነው– እውነትን የመድፍጠጥ አቅምና ሃይል ባይኖረውም፡፡ አዎ! መልክ፣ ቀለም፣ ስያሜውና አመጣጡ ለየቅል ሊሆን ይችላል እንጂ፣ የታዳጊ ሀገራትን አስተሳሰቦችና የልማት

አጀንዳዎች ለማኮስመን ከየጥጋጥጉ ሂሳብ እየቀመሩ ለዘመናዊ እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ዘመቻ ምቹ አውድ የሚሆናቸውን አጋጣሚ ለመፍጠር የመውተረተሩ ፅንፈኞች መኖራቸው የግድ ነው፡፡

ግና የፀረ - ታዳጊ ሀገራትን ልማት በአካባቢና ጥበቃና በሰብዓዊ መብት ጥሰት ስም ጥላሸት ለመቀባት የሚሞክሩ የአሮጌ ርዕዮተ- ዓለም አራማጆችን የተመሰጠረ ሴራ ለማጤን እጅግ ቀላል ነው። አዎ! ነባራዊው ዓለምም ሆነ ታሪክ እንደሚነግረን፤ የአክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች ድብቅ አጀንዳ “የሆድ ጉዳይ” እንዲሁም የሸመገለ የፖለቲካ ፍልስፍና ገመድ ትስስር ስብቀት መሆኑን ለመረዳት ብዙ መጠየቅና መመራመር አያስፈልግም፡፡ ገመዱን በጣጥሰውና ከሸምቀቆው የወጡትን የቻይናን፣ የህድንና የኮሪያን ህዝቦች ማስታወስ ብቻ በቂ ይመስለኛል፡፡ በራሳቸው የፖለቲካል-ኢኮኖሚ መስመር ተጉዘው ኒዮ-ሊበራሊዝምን ድል በመንሳት ለዛሬው ማንነታቸው በቅተዋልና። ሀገራችንን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ ሀገራትም ከነባራዊ ተጨባጭ ሁኔታቸው በመነሳት በነደፏቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ፈጣንና ተከታታይ ዕድገት እያስመዘገቡ በመሆናቸው፤ አክራሪ ኒዮ-ለበራል ሃይሎች እንደ ሳልሳዊ ጊቤ ዓይነት ፕሮጀክቶችን የመኮነን አጀንዳቸው አዲስ አበቤዎች እንደሚሉት “የተበላ ዕቁብ” ስለሆነ ለቀቅ ቢያደርጉን መልካም ነው—ለ“ዳቦ” እና ሸምግሎ እየናወዘ ላለው አዛውንቱ ኒዮ-ሊበራሊዝም ፖለቲካል-ኢኖሚ ፍልስፍና ስርየት ሲባል የሚለፈፍን የቁራ ጩኸት የሚያዳምጥ የለምና። ቸር እንሰንብት።